# የኢትዮጵያ ዘውድ ምክር ቤት

**THE CROWN COUNCIL OF ETHIOPIA**

## ስለ ኢትዮጵያ ወቅታዊ ሁኔታ የተሰጠ መግለጫ

ከክቡር ልዑል ኤርሚያስ ሳህለሥላሴ፤ የኢትዮጵያ ዘውድ ምክርቤት ፕሬዘዳንት

ዋሺንግተን ዲሲ፤ የካቲት 15 ቀን 2010 ዓ.ም

በወቅቱ ወዷ ኢትዮጵያ፤ በታላቅ አዳጋና ችግር ላይ ትገኛለች። ይህ ታሪካዊ ሰአት፤ ሁሉም ኢትዮጵያውያን ቆም ብለው በጽሞና እንዲያስቡ ከፍተኛ ጥሪ የሚያስተጋባበት ነው። ይህ ግዜ አንድነት፤ ተስፋና ጥሩ አመራር የምንመርጥበት ወይም እርስበርስ የምንጣላበትና ከ3ሺ ዓመታት በፊት የተጀመርነውን ታላቁን የሀገር ግንባታ ዕቅድ የምናጠፋበት ሊሆን ይችላል። አሚራጩ ራሳችንን ታላቅ አስተዋይና አዙረን የምናይ ኢትዮጵያውያን መሆናችንን የምናረጋግጥበት ወይም ተበታትነን ትናንሽ ህዝቦች የምንሆንበትን ሁኔታ መምረጥ ነው።

አሁን ያለንበት ሰዓት፤ ችግራችንንና የሚያንዣንብበውን አዳጋ ለመቋቋም የምንዘጋጅበት እንደዚሁም አንድነታችንንም ሆነ ብልጽግናችንን ለማዳበር ዝግጁ መሆናችንን ለአፍሪካም ሆነ ለመላው ዓለም ህዝብ የምናሳይበት መሆን አለበት።

አባቶቻችን ነጻነታችንን ጠብቀው፤ የሰለሞናዊውን ዙፋን ከትውልድ ወደ ትውልድ አስተላልፈዋል። የሰለሞናዊው ዙፋንም፤ ኢትዮጵያ ብዛት ያላቸው ህብረተሰቦች መኩሪያ እንድትሆንና የህዝቦቿም አንድነትና ክብር እንዲጠበቅ ትልቅ አስተዋጽኦ አድርጓል። የኢትዮጵያ ዘውድ ምክርቤት እነዚህ ለረጅም ግዜ የቆዩና የተፈተኑ ባህሎቻችን መቀጠል እንዳለባቸው ያለጥርጥር ያምናል።

የኢትዮጵያ ዘውድ ምክርቤት የፖለቲካ አቋም በገለልተኝነት ላይ የተመሰረኮዘ በመሆኑ፤ ታላቋን ሀገራችንን መጥፎ አዳጋ ላይ እንዳንጥል ምክር የማስጠት ሚና ይኖረዋል። በግለሰቦችና በብሄረሰቦች መካከል ልዩነቶች እንዳሉ እናውቃለን። ሆኖምግን እነዚህ ልዩነቶቻችን ሊፈቱ የሚችሉት፤ በጥንቃቄና በመተሳሰብ እንጂ በጥላቻና በቁጣ መሆን የለበትም እንላለን።

ብዙ የውጭ ሀይሎች፤ በሀገራችን ወስጥ ስምምነት እንዳይኖርና ኢትዮጵያ እንድትበታተን እንደዚሁም ኢትዮጵያዊነታችንን እንድንጠራጠር ፈልገው፤ እሳት በመጫር ላይ መሆናቸውን መረዳት አለብን። በአንዳንድ ቅሬታዎቻችን ላይ ተመርኩዘው ሊያሳስቱንና ለረጅም ግዜ የሚወስድ ችግር ላይ ሊጥሉን የሚዣኩሩ ሀዪሎችን

በጥንቃቄ መቋቋም አለብን። ከሁሉም በላይ፤ እኛ የአብርሃም ዘሮች የሆንነው ኢትዮጵያወያን፤ ታላቋ ኢትዮጵያ ከእግዚአብሔር ጋር ያላትን ፍቅርና ቃል-ኪዳን ሁልግዜም ማስታወስ ይገባናል።

በእርግጥ፤ በሀገር ፖለቲካ ላይ የተመረኮዘ ቅሬታ ሊኖርብን ይችላል። ይህንን ቅሬታችንን ልናስወግድ የምንችለው፤ የዲሞክራሲ ተቋሞችን በማቋቋምና በማዳበር ብቻ ነው። ለግዜው ግን፤ የተዎራረስነውን ማንነታችንንና ከሁሉም አቅጣጫ መጥተን የፈጠርነውን አንድነታችንን እንደዚሁም ልዩ ህዝብ የሚያደርገንን የአምላክ ጸጋ ተጎናጽፈን የመቻቻል፤ የመደጋገፍ፤ የመረዳዳትና ከእርስበርስ የመማር ፍላጎታችንን መቀጠል አለብን።

ማብታተናችንንና ማለያየታችንን የሚወዱ፤ በሀገራችን ኢትዮጵያ ረጅምና አኩሪ ታሪክ የቀኑና ሀገርነቷ እንዲጠፋ የሚፈልጉ ብቻ ናቸው። ይህ ከሆነ፤ ተጠቃሚዎቹ የሀገራችንን ድክመትና ወድቀት የሚመኙት ብቻ መሆናቸውን እንገንዘብ።

ወድ ኢትዮጵያወያን፤ በጽሞና ስሙኝ። ለፈታተኗችሁ ለሚሞክሩት ሁሉ፤ ርህራሄና ትግስት አሳዩአቸው። ከ3ሺ አመታት በፊት የጀመርነውን የኢትዮጵያን የታላቅነት ግንባታ እንቀጥል። አእምሯችን ቸር እንዲያስብ፤ ልባችን እንዲራራ እንጸልይ። አንድ ላይ ሆነን፤ የተወሳሰበውን ማንነታችንንና እሴታችንን እናዳብር። በብሄረሰቦቻችን መካከል ሊኖሩ የሚችሉት ልዩነቶች፤ በአንድ ቤተሰብ መካከል ያሉና ሚፈታትም የሚችሉ መሆናቸውን እንገንዘብ። ቤተሰብን ከማጥፋት የባሰ ምንምችግር የለም። በብሄረሰቦቻችን ወስጥ ሊኖሩ የሚችሉት ልዩነቶች፤ ሊያሻሽሉንና የበለጠሊያከሩን የሚችሉ እንጂ የሚጎዱን እንዳልሆኑ ለማየትና ለመረዳት እንብቃ።

ቸሩ እግዚአብሔር ኢትዮጵያን ለዘላለም ይጠብቃት።